

# ሳራ

- አብርሃም የእግዚአብሔር ሰው ነበር። እግዚአብሔርን ያነጋግረዋል። እግዚአብሔርም እርሱን በቀጥታ ያነጋግረው ነበር። እግዚአብሔርም ወደ ኮከቦች እንዲመለከትና መቁጠር ይችል እንደሆነ ይጠይቀዋል። “ከአንተ የሚወጡት ዘር ማንዘሮችህም እንዲሁ አይቆጠሩም፣” አለው። በዚያን ጊዜ አብራምና (ስሙ እንደዚያ ተብሎ ይጠራ ነበርና) ሳራይ ልጆች አልነበሯቸውም። በጣም እያረጁ ቢሄዱም ልጅ ግን አልነበራቸውም።

- ሳራ እግዚአብሔር ልጅ እንዳትወልድ ያደረጋት መሰላት።. ስለዚህ አገልጋይዋ አጋር የእርስዋን ቦታ ተክታ ከአብርሃም ልጅ እንድትወልድ ወሰነች። በዚህ መንገድ የተወለደው ልጅም ስሙ እስማኤል ይባላል።

- በአንድ ወቅት አብርሃም በሚኖርበት አካባቢ ከፍተኛ ድርቅ ስለነበር መላ ቤተሰቡን ይዞ ወደግብፅ ምድር ተጓዘ። ወደ ግብፅ ምድር ሊደርሱ ሲሉ ሚስቱን ሳራን እህቱ እንደሆነች እንጂ ሚስቱ እንደሆነች እንዳትናገር መከራት። እጅግ በጣም ቆንጆ ስለነበረች ግብፃውያን በሚስቴ ምክንያት ይገድሉኛል ብሎ ፈራ። የግብፅ ንጉስ ፈርኦንም ሳራን አስጠራትና ወደቤቱ ወሰዳት። በዚህ ምክንያትም አሰቃቂ ነገሮች በፈርኦን ቤት ላይ መፈፀም ጀመሩ። ፈርኦንም ሳራና አብርሃም እንደዋሹትና ሳራ ሚስቱ እንደሆነች ተረዳ። ፈርኦንም አብርሃምን ቤተሰቡን ይዞ እንዲሄድ ፈቀደለት። በተጨማሪም በጎችን በሬዎችንና ግመሎችን በስጦታ አበረከተለት።

- አብርሃም እንደገና በተመሳሳይ መልኩ ንጉስ አቢሜሌክን ዋሸ። ንጉስ አቢሜሌክ ሳራ የአብርሃም እህት እንደሆነች ስለተነገረው ሚስቱ ሊያደደርጋት አስቦ ነበር። እንደእውነቱ ከሆነ ሳራ ግማሽ እህቱ ናት። ቢሆንም ሚስቱ ናትና የተናገረው ነገር ውሸት ነው። እግዚአብሔር ለአቢሜሌክ በሕልም ተገልጦለት ሳራን የሚያገባት ከሆነ ሙት እንደሚሆን ነገረው። አቢሜሌክም አብርሃምን ለምን እንደዋሸ ከጠየቀውና ከወቀሰው በኋላ አሰናበተው። በተጨማሪም እንስሳትን አገልጋዮችንና በብዙ ሺህ የሚቆጠር ብር ሰጠው።

- አብርሃም የ99 ዓመት ሰው በሚሆንበት ጊዜም እግዚብሔር እንደገና ቃል ኪዳኑን አደሰ። ስሙንም ከአብራም ወደአብርሃም ቀየረለት። እንዲሁም የሚስቱ የሳራይ ስም ሳራ ሆነ።

- አንድ ጊዜ ሶስት ሰዎች ወደ አብርሃም ድንኳን መጡ። ምግብ አቀረበላቸው። ከዚያም ከእርሱ ጋር ጨዋታ ጀመሩ። ሳራ እንደምትወልድም ነገሩት። ከድንኳኑ ውስት ሆና ይህን የአብርሃምንና የሶስቱን ሰዎች ጨዋታ

ስታዳምጥ የነበረችው ሳራ ሳቀች። የሳቀችበት ምክንያትም እርሷ በዚያን ሰዓት 90 ዓመት ሲሆናት አብርሃም ደግሞ የ100 ዓመት ሽማግሌ ነበር! ይህም ልጅ ለመውለድ የሚያስችል እድሜ አልነበረም። ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣው መልእክተኛም፣ “ለመሆኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለ ወይ? ልክ በሚቀጥለው አመት በዚህን ሰዓት ሳራን እጎበኛታለሁ። ወንድ ልጅም ትወልዳለች፣” አላቸው።

- እንዳለውም አደረገ። በ90 ዓመቷ ወንድ ልጅ ወለደች። ስሙንም ይስሐቅ ብላ ጠራችው። ትርጉሙም “ሳቅ” ማለት ነው።

- ሳራ ስትሞት እድሜዋ 127 ዓመት ነበር። ታዲያ ልጇ ይስሐቅ በዚያን ሰዓት የ37 ዓመት ሰው ነበር። አብርሃም በሔብሮን አጠገብ የሚገኝ አንድ መሬት ገዛ። የመሬቱ ባለቤት በነፃ ሊሰጠው ፈልጎ ነበር። አብርሃም ግን የመሬቱን ዋጋ ካልከፈለ በስተቀር በነፃ እንደማይወስድ ነገረው። ሳራንም ከኤፍሮን በገዛው የእርሻ መሬት ላይ በሚገኘው ዋሻ ውስጥ ቀበራት።

- በአዲስ ኪዳን በ1ጴጥ.3:5 – 6 ስለ ሳራ እንዲህ እናነባለን፣ “ እንዲህ በቀድሞ ዘመን በእግዚአብሔር ተስፋ ያደረጉት ቅዱሳት ሴቶች ደግሞ ለባሎቻቸው ሲገዙ ተሸልመው ነበርና፤ እንዲሁም ሣራ ለአብርሃም፡- ጌታ ብላ እየጠራችው ታዘዘችለት፤ እናንተም ከሚያስደነግጥ ነገር አንዳች እንኳ ሳትፈሩ መልካም ብታደርጉ ልጆችዋ ናችሁ።”

*You can read about Sarah in Genesis 21.*

Copyright picture used with permission gospelservices.com

http://gardenofpraise.com